PANORAMA # XVII

# የትዝብት አድማስ

**መጋቢት** 5 2000

***ከራስ ጋር መታረቅና ራስን ነፃ መውጣት፥ ሀገርን ነፃ ለማውጣት መሠረት ነው***

*በርካታ የታሪክ መጻህፍት እንደ መዘገቡትና መላውም ዓለም ሊክደው የማይችለው ሃቅ፥ የኢትዮጵያ ሕዝብ በውጭ ወራሪ ኃይሎች ያልተበገረ መሆኑን ነው:: በተደጋጋሚ ነፃነቱን ሊያሳጡት የመጡትን ቅኝ ገዥዎችና ሌሎች ባዕዳንን ተቋቁሞ በመመለስ የአያሌ ዘመን የነፃነት ልዕልናውን አስከብሮ የቆየ ሕዝብ በመሆኑ፥ ዘለዓለም አንገቱን ሳይደፋ፥ በኩራትና በራስ መተማመን ባኅርይ ማንነቱን አስመስክሮ ኖሯል:: ይህን ሊያደርግ የበቃው፥ በአንድ ምሥጢር ነው:: ይህም ምስጢር፥ ሕዝቡ ሳይከፋፈል ተባብሮና ተረዳድቶ የጋራ ጠላቱን ለመመከት ችሎታና ቆራጥነት ስለነበረው ነው:: በዚህ የታሪክ ሂደት ውስጥ፥ ይህንን አኩሪ ታሪክ ሊያስመዘግብ የበቃው ደግሞ፥ በዘመኑ የነበረው ሕዝብ፥ እያንዳንዱ ዜጋ መጀመሪያ፥ ከራሱ ጋር ፥ ቀጥሎም ከወገኑ ጋር የታረቀና የተስማማ ስለነበር ነበር::: ይህ ባይሆን ኖሮ፥ በዘመናዊ ሥልጣኔ እጅግ በጣም የመነጠቀውንና በጦር ኃይልም ተወዳዳሪ ያልነበረውን የባዕድ ኃይል ሊቋቋም ይችል ነበር ለማለት ይከብዳል:: ታዲያ ከራስ ጋር እየታረቁ፥ ራስንም ነፃ እያወጡ ከወገን ጋር ታርቆና ተስማምቶ መኖር፥ ሀገርንም ነፃ ማውጣት ብቻ ሳይሆን፥ በልማትና ዕድግት ጎዳና ለመገስገስም ዓይነተኛ ዓብነት ይሆናል::*

*የኢትዮጵያ ሕዝብ በታሪኩ፥ ሀገሩን ከባዕድ ወረራ ነፃ አድርጎ ሊቆይ ቢችልም፥ በልማት ጎዳና ተሰማርቶ ወደ ብልፅግና ሊገሰግስ አልቻለም:: ይህም ያለ ምክንያት አልነበረም:: የውስጥ ሠላምና መረጋት፥ ፍትኃዊና ነፃ አስተዳደር፥ አግኝቶ አያውቅም:: ተፈራራቂ ገዥዎቹ፥ በልማትና ዕድገት ቅኝት ውስጥ እንዲገባ አላደረጉትም:: ሆን ብለውም ይሁን ሳያውቁት፥ ሕዝቡን ተስማምቶ እንዲኖር የሚያስችለውን ሁኔታ አይፈጥሩለትም:: አድልዎና የፍርድ መዛባት፥ ጭቆናና አምባገነናዊ ሥርዓት በሕዝቡ ላይ የተጫኑ ቀንበሮች በመሆናቸው፥ ልማትና ዕድገትን አፍነው የያዙት ደንቃራዎች ነበሩ/ናቸውም:: መሪና ተመሪ፥ መንግሥትና ሕዝብ ታርቀውና ተስማምተው አያውቁም:: መሪዎች ነን ባዮቹም፥ እንኳንስ ከሕዝቡ ጋር ከራሳቸው ጋርም ታርቀው አያውቁም:: መሪዎቹና አገዛዞቻቸው፥ ከራሳቸው ጋር ታርቀው ነፃ ያልወጡበትና ሊወጡም የማይችሉበት፥ ዓላማቸውና ባኅርያቸው፥ ለራሳቸው ጥቅምና ምኞት ብቻ ስለቆሙና ከሕዝብ ተፃርረውና ተጣልተው ስለሚኖሩ ስለ ነው:: በሕዝቡ ዘንድ የሚያደርሱበት በደልና ግፍ፥ ጭቆናና ወንጀል እነርሱ*

ራሳቸውን፥ በፍርሀትና በኃጢአት ስንሰለት ተብትቦና ተቀፍድዶ ስለሚያስራቸው፥ ዕድሜያቸውን በሙሉ፥ በጨለማና በስጋት ወኅኔ ቤት ውስጥ ይኖራሉ። በመሆኑም፥ ራሳቸውን ነፃ ባለማውጣታቸው ሕዝብንና ሀገርን ነፃ ማውጣት የሚስችላቸውን ሁለንተናዊ ችሎታ ተነፍገው በባርነት ጭጋግ ውስጥ እየተደናበሩ ያሳልፉታል። የተፈጥሮ ህግ በመሆኑም ጊዚያቸው ሲያከትም፥ ሀገሪቱንና ሕዝቧን ነፃ ሳያወጡ ከስመው ይቀራሉ። ራስን ነፃ ያለማውጣት ችግር በመሪዎች ብቻ የሚወሰን ሳይሆን፥ በተለያዩ የኅብረተስብ ክፍሎች ውስጥ የሚከሰት በሽታ ነው። መፍትሄውም አንድ ብቻ ይመስለናል። ይኸውም፥ በዜግነት ይሁን፥ በኅብረተስብ ደረጃ፥እያንዳንዱ ዜጋ/ ግለሰብ ራሱን ነፃ ማውጣት ያለበት መሆኑን ነው። ራስን ነፃ ማውጣት ሲባል፥ራስንና ኅብረተስብን ብሎም ሀገርን ከሚጎዳ ባኅርይና ድርጊት መቆጠብ ለማለት ነው። የግል ባኅርይና ድርጊት ለኅብረትሰብና ለሀገር የሚጎዳ ከሆነ እዚያው በግለሰብ ደረጃ በራሱ ጓዳ ሊወሰን ይገባል እንጅ፥ ሀገርን እንዲያምስ ሊፈቀድለት አይገባም ለማለት ነው። “ አመልን በጉያ ባተሊነትን በጓዳ” የተባለው ይትብኃልም ይህንን ለመግለፅ እንደሆነ ይታመናል። በተለይ ይህ ራስን ነፃ የማውጣት ኃላፊነትና ግዴታ፥ በፖሊቲካ ድርጅት መሪዎች፥ በምሁራን፥ በአዛውንቱ፥ በደራሲያንና በኃይማኖት አባቶች በኩል ሚዛኑ የከበደ ሊሆን ይገባል ብለን ለማመን እንፈልጋለን። እነኝህ የኅብረተሰብ ክፍሎች፥ እራሳቸው እራሳቸውን ነፃ ማውጣት ካልቻሉ፥ ስለኅብረተሰቡ ደኅንነት ቀርቶ፥ ስለ ራሳቸው ዓላማ እንኳን ቢሆን፥ ቅንጣት ያህል መልካም ተግባር ሊፈጽሙ ይችላሉ ተብለው የሚጠበቁ አይሆኑም። ምክንያቱም፥ በአስተሳሰብም ይሁን በአመለካከት፥ በሞራልም ይሁን፥ በመንፈስ፥ እራሱን ነፃ ያላወጣ ማነኛውም ክፍል፥ ሌላውን ነፃ ለማውጣት የሞራልም ይሁን የሰብዕና፥ ብቃትና ሥልጣን ሊኖረው ስለማይችል ነው። ይኸንን የማይታበል ሀቅ መቀበል ማለት፥ ከሌላው ጋር ለመታረቅ በሚደረገው ጥረት፥ የመጀመሪያው ርምጃ እንደሆነ ይቆጠራል ማለት ነው። የወያኔ መሪዎች ኢትዮጵያን አሰመልክቶ ያላቸው ችግር፥ መጀመሪያውኑም ቢሆን ከራሳቸው ያስተሳሰብ ጠባብነት ነፃ ስለአልወጡ ነው። ታዲያ መጀመሪያ ራሱን ነፃ ያላደረገ፥ እንዲትስ ሌላውን ነፃ ሊያወጣ ይችላል?

ምንም እንኳን ያለፈውን ታሪካችንንና የመንግሥታቱንም ድርጊትና ባኅርይ መጠቃቀሱ ለግንዛቤ ያህል ይረዳ ይሆናል ቢባልም፥ በአመዛኙ ትኩረት ሊሰጠው የሚገባው ግን በወደፊቱ ዕድላችንና ሕይወታችን ላይ መሆኑ አከራካሪ አይሆንም። “ሙታንን ሙታን ይቅበሯቸው” እንደሚባለው፥ የወያኔ መሪዎች የሞቱት፥ ገና ከመጀመሪያው አዲስ አበባ ከመግባታቸው አስቀድሞ፥ የኢትዮጵያን ሰንደቅ ዓላማ ብጣሽ ጨርቅ ካሉበትና ካልተገነጠልን እንሞታለን ብለው ከጮሁበት ወቅት ጀምሮ ነው። ወያኔዎቹ አልተቀበሩም እንጅ በአትዮጵያ ሕዝብ ዘንድ የሞቱት ያኔ ነው። ከራሳቸው ጋርም የተጣሉት ያኔ ነበር። ከራሱ ሕዝብ፥ ታሪክ፥ ባኅል፥ ማንነትና ዕምነት ጋር የተጣላ ማነኛው ክፍል፥ በመሠረቱ የማይታረቅና የማይቀራረብ ችግር አለበት ማለት ነው። መታረቅና መቀራረብ ከሌለ ደግሞ፤ ከሀገር ጋር ቀርቶ ከግል ጓደኛ ጋር አብሮ መኖር ይከብዳል። የወያኔ መሪዎች ከራሳቸው ጋር እየታረቁ ከኢትዮጵያ

*ሕዝብ ጋር መታረቅ እንደሚገባቸው፥ ለአለፉት አስራ ሰባት ዓመታት በቂ ጊዜና ዕድል ተስጥቷቸው ነበር። አልተጠቀሙበትም። የሀገራችንን ሰንደቅ ዓላማ ዛሬም ማዋረዳቸውን ቀጥለውበታል። ከዚህም በላይ፥ ለዘመናት አብሮ የቆየን ሕዝብ ከወገኑ ጋር እየተለያየ እንዲኖር የሚያደርግ የዘረኛ ሥርዓትና ፖሊሲ ያወጡ ኃላፊነት የማይሰማቸውና አጥፊዎች ናቸው። ከራስ ጋር ያለመታረቅ ችግር በሁላችንም ዘንድ ያለ መሆኑን አምነን ተቀብለን፥ ይህን መሠረታዊ- ሀገራዊ እንቅፋት ለማስወገድ ካልጣርን፥ ዘለዓለም በአምባገነኖችና በባዕዳን ኃይሎች ብቻ እያመካኘን ሕይወታችንን መግፋት አንችልም። እራስን እየመረመሩ፥ እየገመገሙ፥ ስህተትን አርሞ፥ ከስህተትም እየተማሩ፥ ከራስና ከሌላው ጋር ታርቆ የጋራ ሀገርን በጋራ የማዳንና የመገንባት ርምጃ ካልጀመሩ፥ በጨቋኞች ሥርዓት ብቻ እያመካኙ ለመኖር መፈለግ፥ መፍትሄ አይሆንም። በተለይ የፖሊቲካ ድርጅት መሪዎች በዚህ ረገድ ከፍተኛ ለውጥ ማድረግ እንዳለበቸው በሕዝቡ ዘንድ ይጠበቅባቸዋል። ይህን ሳያደርጉ ቢቀሩ፥ ሀገር ለመምራት፥ ሕዝብ ለማዳን የሚያበቃቸውን የሞራል ብቃት ማግኘት የሚያስቸግራቸው ይሆናል። እንደ ኢትዮጵያ፥ ባለ ብዙ ፈርጅና የተወሳሰበ ችግር ያላትን ሀገር ለማስተዳደር፥ ምን ያህል አስቸጋሪ መሆኑን ያልተረዳ የፖለቲካ ድርጅት መሪ፥ እራሱን ደጋግሞ መመርመር ይኖርበታል። የኢትዮጵያ ሁለንተናዊ ችግር መፈክር በማነብነብ ብቻ የሚፈታ እንዳልሆነ ከደርግ መማር የሚቻል ይመስለናል። " የቡታ ጅራ ገበሬዎች ማኅበር ተሰብስቦ አሜሪካን ኢምፔርያሊዝምን አስጠነቀቀ" እየተባለ ሲሾፍ የነበረው ቀልድ የመጨረሻው ውጤት ሀገርን ለበላዒ- ሰብ አጋልጦ መፈርጠጥ ሆኖ ነው የቀረው። ነገ ተነገ ወዲያ ኢትዮጵያን እመራለሁ ብሎ የሚያስብ የፖሊቲካ ድርጅት፤ ከአሁኑ፥ ከራሱ ጋር እየታረቀ፥ ከሌሎች የፖሊቲካ ድርጅቶችጋር እየተስማማና ሕዝባዊ ዓላማን አስቀድሞ አሰፈላጊውን የጋራ መሰናዶ ማድረግ ካልተቻለ፥ በኋላ ሰርገኛ መጣ በርበሬ ቀንጥሱ ቢባል መፍትሄ አይመጣም።*

*የኢትዮጵያ ምሁራን፥ በዓይነትም ሆነ በብዛት፥ በጥራትም ሆነ በይዘት፥ ከፍተኛው ደረጃ እንዳላቸው፥ ተደጋግሞ ይነገርላቸዋል። ይህን ሐቅ አስመልክቶ በየተገኘው አጋጣሚ ሁሉ፥ ብዙ እንደተፃፈና እንደተነገረ እናስታውሳለን። እስካሁን ግን ከራሳቸው ጋር እየታረቁ፥ እርስ በእርሳቸው ተስማምተውና ተማምነው ለሀገር የሚበጅ መፍትሄ ለማምጣት አልቻሉም። እንዲያውም እቅጩን እንነጋገር ከተባለ፥ ሁሉን ወካይ ብሔራዊ የኢትዮጵያ ምሁራን ጉባዔ በማድረግ የኢትዮጵያን ስትራተጂያዊ ራዕይ ለመንደፍ የጣሩበትን ወቅት ማስታወስ አንችልም። ራሱ ነፃ ያላወጣ ምሁር፥ ሀገርን ነፃ ለማውጣት የሚሳነው መሆኑ የታወቀ ቢሆንም፥ እስካሁን በእዚህ ደረጃ ያሳለፉትን የግድ የለሽና የምንቸገረኝ ወቅት ጨርሰው፥ ለሀገራቸው የሚጠቅም መፍትሄ ማምጣት ካልቻሉ፥ ተምረው እራሳቸውን ከጨለማ ነፃ አድርገዋል ለማለት ይከብዳል። በእኛ ዕምነት፥ ምሁር ማለት እራሱን ከጨለማ አውጥቶ ወገኖቹን ወደ ብርሃን ውጋገን የሚመራ ነው እንላለን። ይህ ካልሆነ፥ የመሪ ያለህ! የምሁር ያለህ! በማለት የሚጮኸው ሕዝባችን ዘለዓለም እንዳለቀስ ይኖራል። የኢትዮጵያ ሕዝብ፥ የወጭ ወራሪዎቹን ተባብሮ ሀገሩን ነፃ አውጥቶ ቢያቆያትም፥ እርሱ እራሱ ግን ከድኅነት፥ ከርሃብ፤ ከበሽታ፥ ከኋላ ቀርነት ነፃ*

ሊወጣ አልቻለም:: ይህ ደግሞ በወራሪ ኃይሎች ምክንያት ብቻ ነው ልንል አንችልም:: በአምባገነኖች መሪዎቹም ብቻ ላይ ልናመካኝ አንችልም:: ምክንያቱም÷ አምባገነን ምን ጊዜም በታሪክ÷ ሀገርንና ሕዝብን የሚጠቅም ተግባር ሠርቶ ስለማያውቅ ነው:: የኢትዮጵያን ሁለንተናዊ ችግር ሊያስወግዱ የሚጠበቅባቸው÷ የፖለቲካ ድርጅቶች÷ ምሁራን÷ ሀገር ወዳዱ ክፍል÷ የአዛውንቱ÷ የኃይማኖት መሪዎች በጠቅላላውም ሴት- ወንድ ሳይባል ሁሉም ዜጋ እንጅ አምባገነኖች አይደሉም:: ለዚህ ብሔራዊ ተግባር የመጀመሪያው ርምጃ እያንዳዱ ዜጋ ከራሱና ከወገኑ ጋር መታረቅ መጀመር መቻል ይሆናል:: ይህ ካልሆነ÷ ዘለዓለም በጨላማ ውስጥ የምንኖር መሆናችንን መረዳት አለብን:: ሀገር የምትሻው ምሁር ለመለስ አገዛዝ የሚጎነበሰውን ሳይሆን÷ ሀገር ወዳዱንና ከሕዝብ ጎን የሚቆመውንና ለሀገርና ለመብት የሚታገለውን ለማለት ነው::

ዛሬ ሁሉም ዜጋ ሀገራዊ ግዴታ አለበት--ኢትዮጵያን የማዳን:: ትግሉ ተፋፍሟል-- ይበልጥ መጤስ፤ መጋጋም፤ መንደድ ይጠበቅበታል:: ትግሉን ለማፈን የመለስ ጀሌዎች እየተሯሯጡ ይታያሉ :: በውጭ ያለውንም የሕዝብና የድርጅቶችን ተቃውሞ ቢቻለው ለማዳፈን ካልሆነለት ደግሞ ለማዳከም÷ በአሁኑ ወቅት የወያኔ ከፋፋይ ቡድን በየቦታው በመንቀሳቀስ ላይ እንደሚገኝ ተደርሶበታል:: የተቃዋሚ ድርጅቶችን ሁሉ ቅስም ለመስበርና÷ ዋጋ ለማሳጣት የወያኔ ደላላዎች ይህ ነው የማይባል የመሰሪነት ሥራ እየሰሩ እንደሆነ በሰደት የሚኖረው ኢትዮጵያዊ ሁሉ ደርሶበታል:: ይህ የውጭ ደላሎች ስብስብ÷ ምሁር ነን ታገይ ነን በሚሉ ጥቂት ባንዳዎች እየተደገፈ ነው:: የሕዝብ ክንድ ይላላና ይደክም ዘንድ÷ በከፋፋይ ሴራ የተሰማሩትን ነቅቶ በመጠበቅ ትግሉን መከላከል ብቻ ሳይሆን÷ የመለስን ሰላዮች እየመነጠረ ማጋለጥ አለበት:: የተቃዋሚ ኃይሎችም ሳይወዱ በግድ የሚተባበሩበት ወቅት መሆኑን ተረድተው÷ እርስ በእርስ ከመራኮት ተቆጥበው ኃይላቸውን በማስተባበር የጋራ ጠላታቸውን መመከትና ማሳፈር አለባቸው:: “ሰርገኛ መጣ ቃሪያ ቀንጥሱ” ቢባል ኋላ የሚጠቅም አይመስለንም:: ዘረኛው ቡድንና ጭፍሮቹ ሕዝብን ሊከፋፍሉ ከመቸውም ጊዜ በበለጠ እየጣሩ ናቸውና! ሕዝብ ግን አንድነቱን ጠብቆ፤ኢትዮጵያዊነቱን አስከብሮ የመለስን ቡድን ለአንዴም ለሁሌም ለማስወገድ አስፈላጊውን መስዋዕት ለመክፈል ዝግጁ ሆኖ መገኘት አለበት:: የሕዝብ አሸናፊነት የታመነበት ነው-- አቸናፊ ለመሆን ግን መታገል መቅደም እንዳለበት ምን ጊዜም መረሳት የለበትም:: ለዚህ መሠረቱ ግን ከወገን ጋር እየተስማሙ በጋራ ዓላማና ብሄራዊ አጀንዳ ዙሪያ ተሰባስቦ በጋራ መታገል ብቻ ነው::

ወያኔ÷ “የሀገር ውስጥ ተቃዋሚውን ሁሉ በቁጥጥሪ ስር አውየዋለሁ÷ አሁን ያስቸገረኝ ዲያስፖራው ብቻ ነው” ብሎ ልቡ ውልቅ ስላለ÷ መጠነ ሰፊ የሆነ የሀገሪቱን ገንዘብ በማፍሰስ የውጭ ዜጎችን ያቀፈ የደላላ÷ (ሎቢይስቶች) ቡድን በመቅጠር የውጩን ኃይል ለማደከም እየተሯሯጠ መሆኑ ሁሉም ደርሶበታል:: ልብ ያለው ልብ ይበል! ሀገር ወዳዱና የተቃዋሚ ድርጅት ሁሉ ከራሱ ጋር እየታረቀ÷ እርስ በዕርሱም እየታረቀና እየተስማማ÷ እራሱን

**ከጥቃት ሀገሩን ከጥፋት እንዲያድን ጥሪያችንን አናስተላልፋለን፡፡ “ለበልጎ አይመክሩም፥ ለአንበሳ አይመትሩም” ነውና ምሥጢራችንን በጉያ፥ ስንቃችንን ባህያ አድርገን፥ ከተት መክት በለን የወያኔን መሰሪ ተንኮልና ጥቃት ማክሸፍ አስፈላጊ፥ አጣዳፊና አንገብጋቢ መሆኑን መርሳት የለብንም!!!**